# እውነት መንፈሳዊ ጋዜጣ



# ርዕሰ አንቀጽ

እግዚአብሔር የሕዝቡ እረኛ ነው። በልጁ ደም የተዋጀን እኛ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የሰራውን ሥራ በማመናችን ያገኘነው አንዱ እና ትልቁ በረከት ደህንነታችን ነው የነፍሳችን ቤዛ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ የገባልን የተስፋ ቃል ደግሞ አስተማማኝ ዋስትናችን ነው። “እስከ ዓለም ፍፃሜ ድረስ እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ” ይህንን ሁላችንም ከፊታችን ባሳለፍናቸው ዓመታቶች በተግባር አይተናል። መልካም እረኛ እንደሆነልን በእያንዳንዳችን ሕይወት የታየ እውነት ነው። ከሁሉም በላይ አስገራሚው ነገር በክርስቶስ ያገኘነውን ሕይወት ሳንጥል አካሉ ከሆነው ሕዝቡ ጋር እያመለክን እያገለገልን በቤቱ መኖራችን አንዱ ነው፤ ይህ በኛ ጥረትና ትጋት ብቻ የሆነ ሳይሆን በጌታ ኢየሱስ አስተማማኝ ክንድ በመደገፋችን ነው እንግዲያውስ ያደረገልንን መልካሙን ነገር በመቁጠር ብቻ አናበቃም፤ እኛ ደግሞ ለእርሱ የሆነውን እናስብ እንደሚገባ በመመላለስ ነው ወይ አመቱን ያሳለፍኩት ብለን እራሳችንን እንጠይቅ፤ ደግሞም ክርስቶስን በሕይወቴ አሳይቻለሁ ወይ በተሰጠኝስ ፀጋ የተቀበልኩትን አደራ በታማኝነትና በትጋት ተወጥቻለሁ ወይ በፀሎት በመጋደል ቃሉን በመመገብ በመኖር ከቅዱሳን ጋር ሕብረት በማድረግ የማዳኑን ቃል በሞት ጥላ ውስጥ ላሉ በማዳረስ ምን ያህል ተግቻለሁ ብለን እራሳችንን ልንገመግም ይገባል። እስኪ ቆም ብለን ጌታ በሚያየን እይታ እራሳችንን እንፈትን እንመርምር ባለፈው ስንፍና እና አለማስተዋል ላለመቀጠል በአዲስ መንፈስና ሃይል ታድሰን የተሻለ ሕይወት ለመኖር እንነሳ ዘንድ ሊመረምረን ያለንበትን ሊያሳየን ከጠማማ መንገድ ሊመልሰን ለሚችል ለመንፈስ ቅዱስ እራሳችንን እና የገባንበትን አዲስ ዓመት አሳልፈን እንስጥ እርሱ ወደ እውነት ሁሉ በመምራት የታመነ ነውና። በመጨረሻ አዲሱ ዓመት የድል እና የበረከት ዓመት ይሁንልን አሜን።

የቤተ-ክርስቲያኒቷ መልዕክት



# በውስጥ ገጾች

- ❖ <u>ዕርሰ አንቀጽ፤</u>

በልጁ ደም የተዋጀን እኛ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የሰራውን ሥራ በማመናችን ያገኘነው አንዱ እና ትልቁ በረከት ደህንነታችን ነው

- ❖ <u>የታንክስጊቪንግ ውሎ፤</u>

የሰማይና የምድር ፈጣሪ ትልቁ እግዚአብሔር እጅግ ታናሽ በሆነ ጉባኤ መካከል ከተገኘ ከዚህ በላይ ስኬት ምንድ ነው፤

- ❖ <u>ስጦታ ሰጭውን እንዳይሸፍንብን፤</u>
  - ግን ምን ያደርጋል ሰለሞን ከጌታ ጠይቆ የተቀበለው ጥበት ትልቁን ጥበብ አስጣለው፤

- ❖ <u>የቤተ ክርስቲያ ዓላማ፤</u>

በነገር ሁሉ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ እንደግ፤

- ❖ <u>ተናገር ዝም አትበል፤</u>

ታድያ የኛ ዘመን ዙሪያው ገባው ሲታይ
ኃጢያት ጽድቅ መስሎት ቆሚል አደባባይ
የሚገልጠው ጠፍቶ እርቃኑን የሚያሳይ
ስንቶች በደጅ ቀሩ ታንቀው በአታላይ፤

በቦስተን የምትገኘው የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ የምታምን የክርስቶስ ኢየሱስን የማዳን ወንጌል ባገኘችው አጋጣሚ ሁሉ የምታሰራጭ ቤ/ክ ነች። ይህም ጋዜጣ ወንጌልን ከምታሰራጭባቸው መንገዶች አንዱ ሲሆን በቤ/ክ የሥነ-ጽሁፍ አገልግሎት አባላት እየተዘጋጀ በየሁለት ወር አንድ ጊዜ ይቀርባል።

የቤተክርስቲያኒቱ መጋቢ
ፓስተር ምሕረቱ ሌጂቦ
Email Meheretu2614@Yahoo.com
Telephone 617-792-5764

ዋናአዘጋጅ.....................ሄኖክ ተሾመ
ምክትል አዘጋጅ........ሐብታሙ አስረስ
የውብዳር ፍሰሐ
ኮምፒዩተር ጽሑፍ.....ትርሲት ጥላሁን
የፊትገጽዲዛይነር.........ዝግጅት ክፍሉ

ለቀጣዩ እትም ይረዳ ዘንድ የእናንተ ተሳትፎ ወሳኝ ሚና ስላለው በሚቀጥለው አድራሻ ያላችሁን አስተያየትና ጥያቄ ላኩልን።

አድራሻ
Ethiopian Evangelical Church in Boston
88 Tremont Street
Boston, MA 02108
Tel. 617-816-8827
E-mail: Henokekka@yahoo.com



# የታንክስ ጊቪንግ ውሎ

ውሎህ የኑሮ ዘይቤህ ምሶሶ ነው መልካም ከሆነ ልትቀናበት ክፉ ከሆነ ልትጠፋበት ግድ ነው ውሎ ይቀርጽሃል ለክፉ ወይንም ለደግ ያበጃጅአል ብዙ ሰዎች በፍጹም ባልጠበቁት መንገድ እራሳቸውን በውሏቸው ውስጥ ተቀርጸው አይተውታል፤ ታድያ ክፉ ጓደኛ ክፉትን ያወርሳል እንዲሉ እንዲሁ መልካም ጓደኛ መልካምን ነገር ያወርሳል፤ ታድያ እኛም በዝች አራት ቀን የታንኪስ ጊቪንግ ውሎ እግዚአብሔር በመልካም ሲቀርጸን ሰንብቷል በቀረው ዘመናችንም የእለት ተእለት ውሏችን ከእግዚአብሔር ጋር ቢሆን ወዳጅነታችንን ብናጠናክር ጢጋ ጥግት ብንል ከእግዚአብሔር ዘንድ መልካምነት እንጠግባለን። ከኖቬምበር 27 ሐሙስ ተጀምሮ እሁድ ኖቬምበር 30 ማምሻውን ማእድ አብሮ በመቁረስ የተጠናቀቀውን 2008 የታንክስ ጊቪንግ ውሎ እጅግ የተዋጣለት ነበር ማለት ይቻላል የእግዚአብሔር መገኘት በግልጽ ሕዝቡን በመባረክ የታየ ሲሆን ብዙ ሰዎች ተጽናንተዋል ተዳሰሰዋል በእርግጥ እግዚአብሔር በመካከላችን ነበር ሲሉ ተደምጠዋል፤ አንድን ኘሮግራም የተዋጣለን ነበር ከሚያሰኙት ነገሮች አንዱ እና ዋናው የእግዚአብሔር በዚያ ጉባኤ መካከል መገኘቱ ነው። የሰማይ እና የምድር ፈጣሪ ትልቁ እግዚአብሔር እጅግ ታናሽ በሆነ ጉባዔ መካከል ከተገኘ ከዚህ በላይ ስኬት ምንድነው እግዚአብሔር ከቸርነቱ የተነሳ በመካከላችን ተገኝቷል እና ስሙ ለዘላለም ብሩክ ይሁን። እንዲ ሲባል በአንዳንድ ሰዎች ልብ ውስጥ እግዚአብሔር ለመገኘቱ ማረጋገጫው ምንድነው የሚል ጥያቄ ሊፈጠር ይችላል የእግዚአብሔር በመካከላችን ለመገኘቱ አንዱ እና ትልቁ ማረጋገጫው ቅዱስ መንፈሱ በዝማሬ እና በአምልኮ ደግሞም የቃሉን እውነት ለሕዝብ በመግለጽ በሙላት መመላለሱ ነው ከዚህም የተነሳ ብዙዎች ተጽናንተዋል ትልቁና ዋናው የእግዚአብሔር አጀንዳ ወንጌል ያለመከልከል በሃይል በባሪያዎቹ በኩል ተገልጧል ይህ ከሆነ በእርግጥ እግዚአብሔር በመካላችን ነበር ቃሉም የሚያረጋግጥልን ይህንን ነው እግዚአብሔር ባለበት አርነት አለ ሰዎች ይጽናናሉ ይፈወሳሉ ይማራሉ ብዙ ማለት ይቻላል እግዚአብሔር ከተገኘ ሁሉ አለና በብዙዎቻችን አእምሮ ውስጥ ሁለት እንኳር የእግዚአብሔር አጀንዳዎች ተጠርዘው ገብተዋል 1ኛ ወንጌልን ላልሰሙ ማሰማት 2ኛ የወንጌል ማሕበርተኛ መሆን የሚባሉ፤

ወንጌልን ላልሰሙ ለማሰማት ምን ዓይነት ዘዴ መጠቀም እንዳለብን ሰፋ እና ዘርዘር ያለ አስደናቂ ትምህርት ተሰጥቶናል ወደፊት ቤተክርስቲያን ይህንን ትምህርት በሲዲ አዘጋጅታ ለምእመናን እንደምታቀርብ ከመሪዎች አካባቢ ሰምተናል ሁላችንም ሲዲውን በመግዛት በእውነት በነፍስ ወከፍ ወንጌልን እንዴት ማሰራጨት እንዳለብን በደንብ ልናውቅ ይገባል። ፓስተር ሰለሞን በአራት ቀን በሰጡት ትምህርት ውስጥ የአጠቃላይ የመልእክቶቿ መልእቅ የሆኑትን ነጥቦች እንደሚከተለው አቅርበነዋል። የወንጌልን ጉዳይ ላፍታ ቸል ልንለው የማይገባ ጉዳይ ነው። ምክንያቱም አሉ አደራውን የሰጠን የሰማይ አምላክ እግዚአብሔር ስለሆነ። እኛ የዳንን ክርስቲያኖች የወንጌል ባለአደራዎች ነን፤ ስለዚህ ስለ ጌታ ከመመስከራችን በፊት ልናውቅ የሚገባን ሶስት ነጥቦች፤ 1ኛ የጌታ ምስክሮች ስለሚኖራቸው አቋም፤ 2ኛ የጌታ ምስክር ለመሆን የሚያበቁ ነገሮች ምንድናቸው፤ 3ኛ በነፍስ ወከፍ ወንጌልን ስለማዳረስ እነዚህን ማወቅ ግድ ነው ሲሉ በአጽኖት ተናግረዋል።

- ስለጌታ ለመመስከር ከማን ጋር ነው የምንሰራው፤
- በድፍረት ወጥተን እንዳንመሰክር ሰበብ የሆኑብን ነገሮች ምንድ ናቸው?
- ስለ ጌታ ለመመስከር ከየት መጀመር አለብን?
- የምንመሰክርላቸውን ሰዎች እንዴት ነው የምንቀርባቸው?
- ምን አይነት ሰዎች ሊገጥሙን ይችላሉ ?
- ለመመስከር ስንወጣ ልንከተላቸው የሚገቡ መመሪያዎች፤
- የመሰከርንላቸውንሰዎች እንዴት ነው የምንከታተላቸው፤
- ጌታንስ ከተቀበሉ (ከዳኑ) በኋላ እንዴት ነው የምንከታተላቸው የሚሉ ነበሩ፤
- እነዚህ ነጥቦች አንድን ክርስቲያ ከመመስከሩ በፊት የሚመሰክርበትን ዓላማ እንዲገነዘብና የወንጌልን ጉዳይ በፍጹም ቸል እንዳይል ያደረጉታል።

በእውነት ለመናገር ሰዎች ወንጌልን ባንመሰክር ምን ያህል ጨካኞችንደሆንን በትምህርታቸው በግልጽ

አሳይተውናል፤ ስለ እሳቸው እግዚአብሔርን እጅግ አድርገን ልናመሰግን ይገባል ሌላው የወንጌል ማሕበርተኛ ስለመሆን ያስተማሩት ትምህርት ድንቅ ነው በእርግጥ ወንጌል እንዲሰፋ በብዙዎች ከሲኦል እንዲያመልጡ የኛ የወንጌል ማህበርተኛ መሆን ትልቅ ሚና አለው ልብ ብላችሁ ከሆነ ብዙ ሰዎች የአንድን የፖለቲካ ድርጅት ዓላማ ከደገፉ በጉለበትና በገንዘባቸው አልፈው እስከ ሕይወት መስዋእትነት ለቆሙለት ዓላማ ሲከፍሉ አይተናል ከታሪክም ብዙ ተምረናል፤ ታድያ ሰዎች በመደረግ ለሚያልፍ ለምድራዊ ፖለቲካ ይህን ያህል ዋጋ ከከፈሉ እኛ ለገባን ለእግዚአብሔር እውነት የወንጌል ማሕበርተኛ ሆነን ዋጋ የማንከፍልበት ምክንያቱ ምን ይሆን? የወንጌል ማሕበርተኛ ልንሆን ይገባል፤ በተረፈ በሲዲ የተዘጋጀውን ገዝተን እንጠቀምበት፤ ትልቅ የሕይወት መመሪያ ይሆንልናል። በስተመጨረሻ ይህ ኘሮግራም የተሳካ እንዲሁን በብዙ መልኩ ተሳትፎ ያደረጋችሁ በሙሉ ጌታ አብዝቶ ይባርካችሁ፤ ፖስተር ሰለሞን ከነቤተሰቡ ዘማሪ ሳሙኤል ቤርሳሞን ከነቤተሰቡ ጌታ አብዝቶ ይባርካችሁ። የሰማነውን እግዚአብሔር በልባችን ያኑርልን።

ከዝግጅት ክፍሉ፤

## <u>ስጦታ ሰጪውን እንዳይሸፍንብን እንጠንቀቅ፤</u>

አንድ አባት ሁልጊዜ ወደ ቤቱ ሲገባ ልጆቹን በፍቅር እያናገረ ይስማቸዋል፤ ይደባብሳቸዋል፤ እንደሚወዳቸው ይነግራቸዋል፤ ከዚህ የተነሳ ልጆቹ ሁል ጊዜ የአባታቸው መምጣት በፍቅርና በብዙ ናፍቆት ይጠብቁታል። አባታቸው ከፍቅሩ የተነሳ የሚበላ የሚጠጣ ይዞላቸው ይገባ ጀመር፤፡ ይህንንም አብዝቶ ባደረገው ጊዜ ከእርሱ ይልቅ የሚያመጣላቸውን ስጦታ በመናፈቅ አባባ ምን አመጣህልን ይሉት ጀመር። ይህ ሁኔታቸው ያላማረው አባት በዚህ ከቀጠልኩ ይህ የማመጣላቸው ስጦታ እኔን ሳይሸፍንኝ አይቀርም በማለት እንደበፊቱ ባዶ እጁን መግባት ይጀምራል፤፡ ታዲያ ልጆቹ እንደለመዱት አባባ ምን ይዘህልን መጣህ ቢሉት እኔ መጣሁላችሁ ይላቸው ጀመር፤፡ ይህንን በተደጋጋሚ ባደረገው ጊዜ ለመዱትና አባባ መጣህልን ይሉት ጀመር፤፡ ወገኖቼ ዛሬስ በእኛ ህይወት ስጦታ ሰጪውን ሸፍኖብን ይሆን? ይህንን እንድናይ መርጫለሁ። ውድ የእግዚአብሔር ቤተሰቦች በዚህ ዘመን ብዙዎቻችን እግዚአብሔር የሰጠን ከፍታ እግዚአብሔርን ሸፍኖብን አያለሁ፤ ታላላቅ የእግዚአብሔር ሰዎችና አገልጋዮች ባልተጠበቀ ፍጥነት ካሉበት ከፍታ ወደታች የሚያሽቆለቁሉበት አንዱ ምስጢር ይህ ነው ብዬ አስባለሁ። አንዳንዶች በሚያስደንቅ ፀጋ ተገልጠው ሲያገለግሉ እግዚአብሔር ሰው ሰጠን ብለን ገና ከአፋችን ሳንጨርስ የት እንደገቡ እናጣቸዋለን ነገራቸው ተበላሽቶ ፀጋቸው ተላጭቶ ማመን በሚያቅት ውድቀት ውስጥ ይገኛሉ ምክንያቱ ምንድነው ሲባል የአንዳንዶቹ ስጦታ ሰጪውን ሸፍኖባቸው አካሄዱ በመበላቸው ሆኖ ይታያል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለዚህ ጥሩ ምሣሌ ሊሆነን ይችላል ብዬ ያሰብኩት ጠቢቡ ሰለሞን ነው፤፡ በነገራችን ላይ ጠቢቡ ሰለሞን በብዙ ክርስቲያኖች ዘንድ የሚታወቀው በብርቱ ጎኑ ሲሆን ሲሰበክም ሲዘመርም የሰማሁት ስለ ብርታቱ ነው። ታድያ ይህ መልካም ቢሆንም ድካሙም ለትምህርታችን ተጽፎአልና ዛሬ ለጽሁፌ ማእከል ላደርገው ወድጃለሁ፤፡ እግዚአብሔር በአባቱ ምትክ እንዲነግስ ከወንድሙ ከአዶኒያስ ነጥቆ ዙፋንን እንደሰጠው 1ኛ ነገሥ ላይ ተጽፎ እናገኛለን።ሰለሞን መንገስ በጀመረ ጊዜ ገና ብላቴና ነበርና እግዚአብሔር ሊረዳው ስለወደደ ምን አደርግልህ ዘንድ ትወዳለህ ባለው ጊዜ የሰጠኸኝን ሕዝብ የምመራበት ጥበብ አለው፤፡እግዚአብሔርም በጥያቄው ስለተደነቀ ከጠየቀው በተጨማሪ ብዙ ባለጠግነት እና ዝና ሰጠው። ከእርሱ በፊትም ሆነ ከእርሱ በኋላ እንደእርሱ ያለ ጥበበኛ እስከማይገኝ ድረስ ባረከው ከዚህም የተነሣ ሰለሞን በአጭር ጊዜ ውስጥ በዓለም ዙሪያ በጥበቡና በባለጠግነቱ በጣም ታዋቂ ሆነ ዝናውም በምድር ሁሉ ወጣ እግዚአብሔር ከሰጠው ጥበብ የተነሣ ብዙ ነገስታት የእርሱን ጥበብ ለመስማትና ለማየት ከዓለም ዙሪያ ይጎርፉ ጀመር፤፡ **ግን ምን ያደርጋል ሰለሞን ከጌታ ጠይቆ የተቀበለው ጥበብ ትልቁን ጥበብ አስጣለው እንጂ፤፡** የእግዚአብሔር ቃል የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ እግዚአብሔርና መፍራት ነው ይላል፤፡ ታድያ ሰለሞን እግዚአብሔርን መፍራት ከእርሱ ራቀ ፊቱን ከጌታ መለሰ ሁለት ጊዜ ተገልጦ ጣኦት እንዳያመልክ ከአዘዘው እግዚአብሔር ሸሸ ከጥበቡ የተነሳ ስሙና ተቀባይነቱ በዓለም ሁሉ ስለገነነ ሁሉን በእጁ ማድረግ ፈለገ ደስ ያሰኘውን ያደርግ ስለነበረ እግዚአብሔርን አስቆጣው በዘመናት ሁሉ ከእግዚአብሔር

*ሕዝብ ጋር ጠላት ከሆኑ ግብጻውያን ሞአባዊያን፤ አሞናዊያን፤ ኤዶማዉያን፤ ሲዶናዊያንና ኬጢያውያን ሴቶች ጋር በፍቅር ተጣበቀ፤ በትዳርም ተቆራኝቶ አማልክቶቻቸውን አመለከ በዘመኑም ሰባት መቶ ሚስቶችና ሶስት መቶ እቁባቶች ነበሩት በኢየሩሳሌም ፊት ለፊት ባለው በተቀደሰው በእግዚአብሔር ተራራ ላይ ካሞሽና ሞሎክ ለተባሉ ለሞአባውያንና ለአሞናውያን ጣኦታት መስገጃን አሰራላቸው። ልቡን ሙሉ በሙሉ ከአምላኩ እግዚአብሔር አራቀ፤፡1ኛነገ 11፡1-10 ስጦታ ሰጪውን ሸፈነበት የመከበሩን ምንጭ ዘንግቶ በአሳዛኝ ሁኔታ ውስጥ ገባ። ወዳጆቼ እኛስ ዛሬ የት እንሆን ይሆን? እስኪ ራሳችንን እንይ የተጻፈው ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፏል ምንአልባት ስጦታ ሰጪውን ሸፍኖብን ይሆን? እናስተውል ብዙዎቻችን በመደረግ በሚያልፍ ነፍሳችንን ግን በማያረካ በዚህ ዓለም ነገር ተውጠናል ፈጥነን እንንቃ ሳናውቀው ክብራችን ጌጣችን የሆነውን ክርስቶስ ኢየሱስን የሚሸፍን ፀጋን የሚላጭ የዚህ ዓለም ክብርና ባለጠግነት ዙሪያችንን ከቦናል በብዙ ጾም ፀሎትና ጩኸት የመጣ ሥራ ከሰጪው በልጦ ቁጭ ብሏል፤፡ ለምን ቤተ ክርስቲያን አትመጣም ስንባል ጌታ የሰጠንን ሥራ  ማሳበቢያ አድርገነዋል ከፍ ያደረገንን ጌታ ለማክበር ጊዜ አጥተናል ድሮ የኘሮግራም ሰዓት እስኪደርስ የሚጨንቀን ሰዎች ዛሬ ግን አርፍደን እንመጣለን ያ አልበቃ ብሎን ቸኩለን እንወጣለን ምነው ስንባል ሥራ አለብኝ እንላለን አንዱ እሁድ ለጌታ መቀደስ አቅቶናል፤ የውጪ እድል ጌታ እንዲከፍትልን በሳምንት ሶስት አራቴ እንዳልጾምንና እንዳልጸለይን ዛሬ ግን ነገር ሲሳካ ሲመቸን ጌታን እንኳን ለማምለክ ቢዚ ነኝ እንላለን፤ በአንድ ወገን ሰርተን ገንዘብ ስናገኝ በሌላ ወገን ደግሞ ክቡር የሆነውን ሕይወታችንን ጥለነዋል፤ ይህንን ስል ግን ሃሳቤን እንደምትረዱኝ ተስፋ አደርጋለሁ ሥራችንን ትተን ኘሮግራም እናሳድ እያልኳችሁ እንዳልሆነ ነገር ግን ሥራ ለሰጠን ጌታ ጊዜ ይኑረን ልል ፈልጌ እንጂ። ሌላ የሚገርመኝ ነገር ደግሞ አንዳንዶቻችን ስልጣኔ በሚመስል ነገር ግን ፀጋን በሚላጭ ዘመናዊነት ተጠምደን ጌታን መስማት አቅቶን ባለመታዘዝ ወጥመድ ውስጥ ገብተን እርሱን ማየት አቅቶናል።ለስንፍናችን ጥቅስ መጥቀስ የስልጣኔ ያህል እየታየ የለበት ዘመን ሆናል። ወገኖቼ እግዚአብሔር ቀን ሳለ ዛሬ ሁላችንን ይመክረናልከምንም በፊት ያከበረንን ጌታ እናክብር እንዲህና እንዲያ እያሉ ምክንያት መደርደር ምንም አይረባንም ጨክነን ለጌታ ጊዜ እንስጥ፤ በሌላ አቅጣጫ ስናይ አንዳዶቻችን ጌታ የአገልግሎት በር እንዲከፍትልንና በፀጋ ስጦታ እንዲባርከን አጥብቀን እንጸልያለን ጌታም የለመነውን ሲሰጠን እንደራሳችን ፈቃድና ምኞት መርጥ እንጀምራለን እውቅና ሲመጣ ተፈላጊነታችን ሲጨምር ቤተክርስቲያን….ሚኒስቴሪ ካልከፈትን እያልን አካኪ ዘራፍ እንላለን። በእርግጥ ራዕይ ከጌታ ከሆነ ጥሩ ነው። ብዙ ሰዎች በራዕያቸው ወጥተው ለቤተ ክርስቲያንና ለምድሪቱ በረከት ሆነዋል ቤተክርስትያንና ሚኒስትሪ መክፈታችን በራሱ ክፋት የለውም የብዙዎቻችን መሻት ግን በከፈትነው ሚኒስትሪና ቤተ ክርስትያን ላይ ጌታ መሆንና መበልጸግ እንጂ ዋጋ ከፍሎ የጌታን ሥራ መሥራት አይደለም። አገልጋይ ማለት ባሪያ ማለት ነው የራሱ የሆነ መብት የሌለው መብቱን በፈቃዱ ለጌታ የሰጠ። እኛ ግን ይህ ይጠፋብናል ከዚህ የተነሳ ብዙ ስንኳዝ አንታይም ነገራችን በመንገድ ይቆማል ወይ ያለፍሬ ዓመታት እናስቆጥራለን ለወንጌል እንቅፋት ሆነን እንኖራለን።የፀጋ ስጦታ ስለተሰጠንና ታዋቂ አገልጋይ ስለሆንን ብቻ ያለ ጌታ ምሪት ቤተክርስቲያን ወይም ሚኒስትሪ ብንከፍት ከጌታ መንገድ ስለሚያወጣን እግዚአብሔርን ሊጋርድብን ይችላል።ሰለሞን ባለማስተዋሉ በእውቅናና በዝና ኀርፍ እንደተወሰደ እንዲሁ በእኛ ላይ እንዳይሆንብን ፈጥኖ መንቃቱ ብልህነት ነው።*

*እንደምታውቁት በዘጸአት መጽሐፍ ላይ የእስራኤል ሕዝብ ከግብጽ ምድር ከፈርኦን ባርነት ነፃ ከወጡ በኋላ በምድረ በዳ የሚበሉት ባጡ ጊዜ በሙሴና በአሮን ላይ በእጅጉ አጉረምርመው ነበር።ይህ ያየ እግዚአብሔር ይህ ሕዝብ በሕጌ ይሄድ ወይንም አይሄድ እንደሆነ አይ ዘንድ እንጀራን ከሰማይ አዘንብለታለሁ ሕዝቡም ወጥተው ለእለት የሚሆናቸውን ይልቀሙ ማንም ከለቀመው ለነገ አያሳድር በስድስተኛው ቀን ደግሞ እጥፍ ይልቀሙ ምክንያቱም ሰባተኛው ቀን የእግዝአብሔር ነውና እረፍት ያድርጉ ብሏቸው ነበር፤ ዘፀ 16፡4-29 የሚገርመው ግን አንዳንዶች ነገን በመፍራት ለነገ አስቀመጡ ግን ሸተተ ከመሸተትም አልፎ ተላ ዘፀ 16፡20 አንዳንዶች ደግሞ በሰንበት ሊለቅሙ ወጡ ግን ምንም አላገኙም ይልቅ እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ ተቆጣ ዘፀ 16፡27-28 ቁጥር 17 ላይ እንዲህ ይላል ብዙ*

ለለቀመ አልተረፈውም ትንሽ ለለቀመም አልጎደለበትም ልብ በሉ እግዚአብሔርን በመስማት ስንኖር ምንም አይጎድልብንም በዚህ ክፍል ላይ እንደምታዩት ሕዝቡ እግዚአብሔርን ካለመስማትና ካልጠግብ ባይነት የተነሳ ምንም ሳይጎድልባቸው ለነገ ሲያሳድሩ ሲተላ በሰንበት ሊለቅሙ ሲወጡ ድካማቸወ ከንቱ ሲሆን ታያላችሁ መጽሐፍ ቅዱስ በዘዳ 33፡27 መኖሪያህ የዘላለም አምላክ ነው የዘላለም ክንዶች ካንተ በታች ናቸው ይላል ስለዚህ ስለስራን አንኖርም ስላልሰራን አንሞትም ብዙዎች ብዙ ሰብስበው መኖር አልቻሉም የሰበሰቡትም ሸቶባቸው ተልቶባቸው ሰላምና ጤናቸውን አሳጥቶ በብዙ ስቃይና መከራ አሉ መገኖቼ የሰበሰብነውን ጌታ ካልባረከው የትም አንደርስም በእርግጥ ሰነፍ መሆን የለብንም ተግተን መስራት አለብን ባለጠግነትም ኃጢያት አይደለም ማጣትም መንፈሳዊነት አይደለም ግን ሥራ ለሰጠን ያገልግሎት በር ለከፈተልን እህልና ወይናችንን ለባረከልን ለእግዝአብሔር ጊዜ ሊኖረን ይገባል፤፡ አልያ ግን ስጦታ ሰጪውን ሸፍኖብን የከበረውን ደህንነታችንን ሊያስጥለን ይችላል። ምንም ዓይነት ሥራ ይኑረን ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ካልገጠመን በቀር ለጌታ ጊዜ ሊኖረን ይገባል፤ ከቃሉ እንዳየነው ሕጌን ይጠብቁ ወይንም አይጠብቁ እንደሆነ አይ ዘንድ እንጀራን ከሰማይ አዘንብላችኋለሁ አለ ጌታ ያየን ዘንድ ሥራን ያገልግሎትና የውጪ እድል የሌላንም በር ከፍቶልን ይሆን? ስለዚህ ሊያየን እንጀራ የሰጠንን ጌታ አሳዝነን እንዳይሆን ዛሬ ቀን ሳለ እንንቃ።

የእግዚአብሔር ሰዎች ሆይ ስለመንገዳችን ጌታን መጠየቅ እንዴት አዋቂነት መሰላችሁ። ንጉሥ ዳዊት በመዝሙሩ እግዚአበሔር ሆይ ና መርምረኝ በደልንስ እንኳን አግኝተህብኝ ቢሆን ማረኝ አለው ማስተዋል ማለት ይህ ነው ሕይወታችንን ስናየው እንደ እስራኤል ሕዝቦች ለነገ ያልነው ላይሸት ላይተላ ይችላል ወይም በሰንበት ልንሰራ ወጥተን ልናገኝ እንችላለን ግን ውስጣችን ተቦርቡሮ ቢሆንስ ገንዘብ ይዘን ቤት ንብረት አፍርተን ግን ባዶነት ቢሰማን የቀደመው መንፈሳዊነታችን ትጋታችን ከጌታ ጋር የነበረን የጠበቀ ግንኙነት ጠፍቶብን ቢሆንስ እስኪ ቆም እንበል ምን አልባትም እንደሰለሞን የሚታይ ጣኦት ላናቆም ወይም ብዙ ሚስቶች ላናገባ እንችላለን ነገር ግን ጌታ በሰጠን ከፍታ ላይ ጣኦት የሆኑብን ብዙ ነገሮች በእያንዳንዳችን ዙሪያ ሊኖሩ ይችላሉ እራሳችንን እንፈትሽ ጌታን የሸፈነብን ከእርሱ በላይ የሆነብን ስንት ጉድ በጓዳችን ገብቶ ይሆን ጠልፎ ሳይጥለን ፈጥነን እንንቃ ወደ እግዚአብሔር አሳብ እንመለስ ስጦታ ከሰጪው በልጦ በአናታችን ላይ ጎጆ እንዳይሰራ ዛሬ ስፍራውን እናሳየው። ንጉሥ ዳዊት በዙፋኑ በሙሉ ክብሩና ሥልጣኑ ላይ ተቀምጦ ሁሉ በእጁ ሆኖ ሳለ እንዲህ አለ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ እዚህ ያደረስከኝ እኔ ማን ነኝ ቤቴስ ምንድን ነው ደግሞ አሁንስ ቢሆን ተስፋዬ ማን ነው አንተ አይደለህምን አለ ልብ በሉ ዳዊት ይህንን ሲናገር እንደ ሰው ተስፋ ሊሆነው የሚችል ብዙ ነገር በዙሪያው አለ ሥልጣን ገንዘብ ዝና ክብር ሌላም ሌላም ሁሉንም ግን ከእግሩ በታች እረግጦ ተስፋ ልትሆኑኝ አትችሉም ለኔ ተስፋዬ ያኔ የበግ እረኛ በነበርኩ ጊዜ ያየኝ በዚያ በምድረ በዳ አባቴ በረሳኝ ጊዜ ያስታወሰኝ አስጠርቶም በታላላቆቼ ፊት ራሴን በዘይት የቀባኝ ከነጥብቆዬ ለንጉሥነት የሾመኝ ያ ጌታ እርሱ ነው አላቸው ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን የገባው የእግዚአብሔር ሰው ስጦታ ሰጪውን ሊሸፍንበት አልቻለም ዳዊት ሁሉ በማን እንደሆነለት ገብቶታል ከዚህ የተነሣ በየእለቱ ለነፍሱ ስለ አምላኩ ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔርን ባርኪ አጥንቶቼም ታላቅ ስሙን ባርኩ እያለ ይሰብካት ነበር ወይ ዳዊት ከትቢያ ከአመድ ያነሳውን እግዚአብሔርን በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ የማይረሳ ሰው ነው። ዛሬም ለእኛ ይህ መንፈስ ይሁንልን የትኛውም ትልቅ የሚመስል በመንፈስ ሲታይ ግን ትንሽ የሆነ ሁሉ ጌታችን አይጋርድብን ከምድረ በዳ ጠርቶ ያከበረንን አመዳችንን ያራገፈልንን ከሰው የቀላቀለንን ጌታ ገብቶን እናምልከው ሲሰጠን ሲያከብረን የበለጠ ክብር የበለጠ አምልኮ ልንሰጠው ይገባል እንጂ በሰጠን ነገር ተውጠን ልናሳዝነው አይገባም። በእውነት በግልጽ እንነጋገር ከተባለ ላከበረን አምላክ ጊዜ ያጣን እርሱ አክብሮን እርሱን ማክበር ያቃተን ተረከዛችንን በእርሱ ላይ ያነሳን ስንቶች ነን የምንበላው የምንጠጣው ያልነበረን በሰው ፊት ለመቅረብ እራፊ ጨርቅ ያጣን ዛሬ ግን ከእርሱ የተነሳ በብዙ ባለጠግነት እና ክብር ደግሞ በከፍታ ያለን ሰዎች በምድረበዳ ደርሶ የታደገንን ጌታ ከፍ ማድረግ ምነው አቃተን ለእርሱስ የነበረን ፍቅር የት ሄደ ስጦታ ሰጪውን ሸፍኖብን እንዳሆን እናስተውል በቤቱ ለአገልግሎት ታማኝ አድርጎ ሲሾመን ምነውሳ እርሱን መስማት አቃተን ለምን

አዋቂነት ተሰማን የሰጠን ክፍታ ለምን እርሱን ሸፈነብን እናስተውል ወገኖች ብዙ ክብር እንዲሆንልን አሁን ካለንበት ክፍታ ክፍታችን እንዲጨምር ዛሬ ስጦታን ከታች ሰጪውን ከላይ በማድረግ አሰላለፉን እናስተካክል እንደ ዳዊት እዚህ ያደረስከኝ እኔ ማን ነኝ ቤቴስ ምንድ ነው እንበለው ይህ መንቃት ደግሞም የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ዳዊት ሲናገር በመልካም ሽምግልና አንቀላፋ ይላል ሽምግልናችን በመልካም እንዲደመደም እግዚአብሔርን መፍራት የነፍሳችን ረሃብ ይሁን። እስኪ ቆም ብለን ራሳችንን እንይ ዛሬስ ስንቶች ነን ጌታ የሰጠንን ይዘን ከጌታ ሃሳብና ፈቃድ የኮበለልን ምን አልባት ከቤተ ክርስቲያን ላንወጣ ጌታንም ላንተው እንችላለን ግን ጌታ የሰጠንን ይዘን ልባችን የኮበለለ በሃሳብ የሸፈትን ቤት ይቁጠረው ንጉሣ ሳኦል ተንቆ የጌታ መንፈስ ከእርሱ እርቆ ለብዙ ዓመታት በዙፋኑ ላይ ተቀመጠ አገልግሎት አለማቆማችን ንግዳችን አለመክሰሩ ከሥራ አለመባረራችን ጌታ ከእኛ ጋር ለመሆኑ ማረጋገጫ አይደለም ሳሆል በዙፋኑ ላይ ቢሆንም የእግዚአብሔር መንፈስ ከእርሱ ጋር እንዳልነበረ ሁሉ ጌታ አብሮ ያለ እየመሰለን ግን በብዙ የተራራቅን ወገኖች ልንኖር እንችላለን እባካችሁ ፈጥነን እንመለስ እግዚአብሔር የክህነት አገልግሎት ለአሮን ዘር ሲሰጥ ክብራቸው ነበር ነገር ግን የዔሊ ልጆች ያከበራቸውን ጌታ ማክበር ሲያቅታቸው የሰጣቸው ክፍታ እርሱን ሲሸፍንባቸው ሲባልጉበት የናቁኝ ይናቃሉ ይህ አይሆንልኝም የሚል ትእዛዝ ከእርሱ ዘንድ ወጣ ሳሙ 2፡30 ወገኖቼ ዛሬ ቀን ሳለ ስጦታ ሰጪውን እንዳይሸፍንብን እናስተውል።ሁላችንን እግዚያብሔ የርዳን

በሂኖክ ተሾመ

## <u>የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን በቦስተን</u>

## <u>የ2009 ራዕይ</u>

“በነገር ሁሉ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ እንደግ” ኤፌ 4፥15

ክርስቶስን በማወቅና በማመን ፈጽሞ ለእርሱ በመሰጠት እርሱን እየመሰልን በነገር ሁሉ ወደ እርሱ እራስ ወደ ሆነው ወደ ክርስቶስ እያደርግ በቃሉ እራሳችንን እየገነባን በፀሎት በመጋደል ክርስቶስ በማመናችን ያገኘነው ሕብረትና አንድነት በማጠናከር የማዳኑን ወንጌል በሞት ጎዳና ላይ ላሉ ለማደረስ እንትጋ።

- ወደዚህ ራዕይ መድረሻ መንገዶች፤

1. የእግዚአብሔር ቃል

ቃሉ ለነገሮቻችን ሁሉ መሠረት ነውና እለት እለት በመንፈስ ቅዱስ በመረዳት ለገባን ለቃሉ እውነት በመኖር መመላለስ፤

2. ህብረት፤

በክርስቶስ የተገኘውን ቤተሰብነትና አንድነት በማወቅና በመጠበቅ በህብረት በማምለክ በማገልገል የክርስቶስን ፍቅር በመንፈስ ቅዱስ ሀይል በመደገፍ በተግባር ለሁሉም በማሳየት አንድም ሰው ብቻውን እንደሆነ እስከማይሰማው ድረስ እርስ በርስ መያያዝ፤

3. ምስክርነት የወንጌል ስርጭት፤

የእግዚአብሔር ዋነኛ ሃሳብ የሆነ ወንጌል የራሳችን ዋነኛ ዓላማ በማድረግ በክርስቶስ ደህንነትን የተቀበልን ሁላችን በየእለቱ በሁሉም ስፍራ ወንጌልን በመናገር የተሰጠንን አደራ በታማኝነት በትጋት ፈጽሞ በመሰጠት በመንፈስ ቅዱስ ሃይል በመታመን አደራችንን መወጣት፤

4. ፀሎት፤

እለት ተለት ከምናመልከው አምላክ ጋር ህብረት በማድረግ ፊቱን በትጋት በመፈለግ የእግዚአብሔርን ክንድ በግል ህይወታችን፤ በህብረታችን፤ በአገልግሎታችና በምድር ላይ እንዲገለጽ በመንፈስ ቅዱስ ሃይል በመታመን መጋደል።

ይህ የቤተክርስቲያን ዓላማ እንደ ቤ/ክ የሁላችን ዓላማ ሊሆን ይገባል፤ በስተመጨረሻ በጌታ ፊት ስንቆም ያለ ማእረግ እንዳንሆን ዛሬ ቀን ሳለ በመክሊታችን እናትርፍበት ይጠበቅብናል የወንጌል ባለ አደራነት የቤክ መሪዎች ወይንም አገልጋዮች ሃላፊነት ብቻ አይደለም የወንጌል ጉዳይ የሁላችን ጉዳይ ነው የእግዚአብሔር አጀንዳ አንድ ብቻ ነው እርሱም ወንጌል ታዲያ ይህ የእግዚአብሔር አጀንዳ የኛም አጀንዳ ሊሆን ግድ ነው፤ አልያ ኑሮ በከንቱ ሆነን እናልፋለን ምናልባት ታሪካችን ሲዘከር እከሌ እከሌን ወለደ ሞተ ሊሆን ይችላል ከዚህ ለመዳን ዛሬ ነቅተን የእግዚአብሔር አጀንዳ ይዘው ከቆሙት ከመሪዎቻችን ጎን በመቆም የእግዚአብሔርን ዓላማ ልናስፈጽም ይጠበቅብናል።

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን በቦስተን
ETHIOPIAN EVANGELICAL CHURCH BOSTON
88 TREMONT STREET, BOSTON, MA, 02108
T: 617-523-5058 F: 617-523-5058
www.eecBoston.org